# አሉ ቧልታይ

-በአበራ ለማ (ኖርዌይ)

ወንፊት ጊንጊልቻ
ታልቋጠረ እንደሰልቻ
ምድቡ ተግትቻ...
አሉ አሉ... አሉ ብቻ፤

አሉ አሉ ወንፊትኛ
ማን ፈቅዶ ሰፌድኛ
አሉ አሉ ጊንጊልቺኛ
ትውን ጭውት ቦዘንኛ
አወይ ስደት አግዳሚኛ
ሁሉን ተርታ ማስተወኛ
መልቲ አንጋሽ ሡልጣንኛ፤

እናም ወንፊት ጊንጊልቻ
ታልቋጠረ እንደሰልቻ
ምድቡ ተግትቻ...
አሉ አሉ... ሽንቁር ብቻ፤

አሉ አሉ የሚከካ
አሉ አሉ የሚቦካ
አወይ ቧልታይ አተዋወን
ሰፌድ የለ የሚለየን
ወንፊትነት ተታደገን
አወይ ስደት፣ እማኝ እልቂ
አሉ ቧልታይ፣ ዳቦ ስንቂ፤

እኮ ወንፊት ጊንጊልቻ
ታልቋጠረ እንደሰልቻ
ምድቡ ተግትቻ...
አሉ አሉ... መስጠት ብቻ፤

አሉ አሉ ወንፊትኛ
ዘሩት አሉ ጊንጊልቺኛ
ዋቤ አልቦ ሽብርተኛ
የባንኮኒ ጦር አርበኛ
ያገር ሕመም ማጠንጠኛ
አሉ ቧልታይ መተወኛ፤
አወይ ስደት አግዳሚኛ
ሁሉን ተርታ ማስተወኛ
መልቲ አንጋሽ ሡልጣንኛ፤

እናም ወንፊት ጊንጊልቻ
ታልቋጠረ እንደሰልቻ
ምድቡ ተግትቻ...
አሉ አሉ... አፋፋቱ ብቻ፤

አሉ አሉ ወንፊትኛ
አሉ አሉ ጊንጊልቺኛ
እውነት ባሰት መገነዣ
ሃቅን በሸፍጥ መከፈኛ
ያገር ችግር ማደንዘዣ
አሉ ቧልታይ በየቤቱ
ማራባቱ ማባዛቱ
መች ይሆን ማብቃቱ?
የዲያስፖራ እንግልቱ
ከሰደት ቤንቹ መለየቱ
ወንፊቱን ትቶ...
ሰፌድ ሰፌዱን መሻቱ
መች ይሆን ሰኬቱ?
አባ ወሬን አባ ወናፌን መግቻ
በመረጃ በሰፌዱ እኩዩን ሁሉ መርቻ?
መች ይሆን መዓልቱ መች ይሆን ለሊቱ
አሉ ቧልታይ ሙቶ፣ ሀቅ መጎልበቱ?

አወይ ሰደት አግዳሚኛ
ሁሉን ተርታ ማስተወኛ
መልቲ አንጋሸ ሡልጣንኛ፤
እናም ወንፊት ጊንጊልቻ
ታልቋጠረ እንደሰልቻ
ምድቡ ተግትቻ...
አሉ አሉ... ወናፍ ብቻ፤